# የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር ----/2016

## ማብራሪያ

ግንቦት 2016

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

nbe.gov.et

# 1. <u>መግቢያ</u>

**ባንኮች ከአገር ዉስጥና ከዉጭ አገር ገንዘብ በማሰባሰብና ለኢንቨስትመንትና ለልማት በማዋል እንዲሁም የክፍያ ሥርዓትንና የገንዘብ ፖሊሲን በማሳለጥ ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ዓይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡** በሌላ በኩል፣ የባንክ ዘርፍ አለመረጋጋት ሕብረተሰቡ በባንኮች ላይ ያለዉ አመኔታ እንዲሸረሸር እና የኢኮኖሚ ቀዉስ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ ይህም በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያሳድረዉ አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በመሆኑም፣ ከሌሎች ዘርፎች በተለየ መልኩ በባንኮች ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ይደረጋል፡፡ ለዚህም ጊዜዉን የዋጀ እና የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ በማዉጣት ተግባራዊ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

**የመጀመሪያዉ ባንክ ከተመሠረተበት እ.ኤ.አ ከ1906 ጀምሮ በአገራችን በርካታ የባንክ ሥራ አዋጆች ወጥተዉ ሥራ ላይ ውለዋል፡፡** በንጉሡ ዘመን የነበሩት በርካታ የአገር ዉስጥና የዉጭ ባንኮች በሶስት የመንግሥት ባንኮች ሥር በመጠቃለል በደርግ ዘመን በዕዝ ሥርዓት እንዲመሩ ተደርገዋል፡፡ በቀጣይም አገሪቱ ወደ ነጻ የገበያ ሥርዓት መሸጋገሯን ተከትሎ በተከናወነዉ የሪፎርም ሥራ  ዘርፉ ለሀገር ዉስጥ የግል ባለሀብቶች ክፍት ሆኖ ቁጥጥር እንዲደረግበት የሚያስችል የባንክ ሥራ ስለመፍቀድና ስለመቆጣጠር አዋጅ ቁጥር 84/1986 ወጥቶ በሥራ ላይ ዉሏል፡፡ ይህ አዋጅ በ2000 ዓ.ም አዳዲስ ጉዳዮችን አካቶ በሥራ ላይ እንዲውል በተደረገው የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 እንዲሻር ተደርጓል፡፡

በቅርቡ በተደረገዉ የፖሊሰ ሪፎርም የዉጭ አገር ዜግነት ያላቸዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን በዘርፉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ፣ በዲጂታል ዘዴዎች የፋይናንስ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች የፋይናንስ ተቋማት እንዲሆኑ እና ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች ኢንዱስትሪዉን እንዲቀላቀሉ የሚያስችል የባንክ ሥራ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 1159/2011 መዉጣቱ ይታወቃል፡፡

በዚህም መሠረት፣ እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት 2016 ድረስ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የወሰዱ ባንኮች ቁጥር 32 የደረሰ ሲሆን፣ ከእነዚህም ሁለቱ የመንግሥት የተቀሩት ሰላሳዎቹ የግል ናቸዉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች 4 ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ 28 መደበኛ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸዉ፡፡ ከዚህም ሌላ፣

የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት የሚሰጡ ባንኮች ቁጥር 18 ደርሷል፡፡ ባንኮች በመላዉ አገሪቱ አገልግሎት የሚሰጡ በድምሩ 12,811 ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርንጫፎች አሏቸዉ፡፡ በተጨማሪም፣ ሌሎች 7 ባንኮች ዘርፉን ለመቀላቀል የምሥረታ ሂደት የጀመሩ ሲሆን በተለያየ ደረጃ ይገኛሉ፡፡

እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት 2016 ድረስ የባንኮቹ ጠቅላላ ሀብት ብር 3.3 ትሪሊዮን፣ ተቀማጭ ገንዘብ ብር 2.4 ትሪሊዮን፣ ብድርና ቦንድ ብር 2.3 ትሪሊዮን እንዲሁም ካፒታል ብር 285.6 ቢሊዮን ደርሷል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ፣ ባንኮች ከወለድ ነጻ እና በዲጂታል ዘዴ የሚሰጧቸዉን አገልግሎቶች አጠናክረዉ የቀጠሉ ሲሆን፣ እንዲሁም ዕድገታቸዉን፣ ጤናማነታቸዉንና ትርፋማነታቸዉን አጠናክረዉ ቀጥለዋል፡፡ የአገራችን የፋይናንስ አካታችነት ምጣኔ 45 በመቶ ደርሷል፡፡

***በሀገራችን ያለዉ የባንክ ዘርፍ ለዉጭ ባለሀብቶች ለበርካታ ዓመታት ዝግ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል***፡፡ የውጭ ባንኮች በዘርፉ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ባለመፈቀዱ በሀገር ውስጥ ባንኮች መካከል ፈጠራ የታከለበት እና በአዳዲስ አገልግሎቶች የታጀበ ውድድር አነስተኛ እንዲሁም ከውጭ ገበያዎችና ኢኮኖሚዎች ጋር ያለዉ ትስስር ዝቅተኛ በመሆኑ ባንኮች ብድርና የዉጭ ምንዛሪ በሚፈለገዉ መጠን ማቅረብ አልቻሉም፡፡ የተደራሽነት ዉስንነት፣ የግለሰቦችንና የተቋማትን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ አገልግሎቶች እጥረት፣ እንዲሁም የፋይናንስ ገበያ መሠረተ ልማት ውስንነት የዘርፉ መገለጫዎች ሆነዉ ቆይተዋል፡፡ ከባንክ ሥራ ዕዉቀት፣ ክህሎት፣ ልምድና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አኳያ የሀገር ውስጥ ባንኮች ገና ይቀራቸዋል፡፡ እ.ኤ.አ እስከ መጋቢት 2016 መጨረሻ (በቅርቡ ወደ ባንክ የተሸጋገሩትን 6 አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ደንበኞች ጨምሮ) አጠቃላይ የባንክ ዘርፍ የብድር አገልግሎት ደንበኞች ብዛት ከ3.1 ሚሊዮን ብዙም ያልዘለለ ሆኖ ተደራሽነቱም በአዲስ አበባ እና በጥቂት ትልልቅ ከተሞችና ተበዳሪዎች ተወስኖ ይገኛል፡፡ ይህም ሀገሪቱ ካላት የህዝብ ብዛት እና የቆዳ ስፋት አኳያ ተደራሽነቱ እጅግ የተወሰነ መሆኑን ያሳያል፡፡

አሁን በሥራ ላይ ያሉ የባንክ ሥራ አዋጆች ማለትም የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 እና የባንክ ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1159/2011 ላለፉት 16 ዓመታት ሲሠራባቸዉ የቆዩ ናቸዉ፡፡ እነዚህ አዋጆች ለባንኮች ጤንነት፣ ዕድገትና አካታችነት ካበረከቱት አስተዋጽዖ አንፃር የማይተካ ሚና ነበራቸው፡፡ ሆኖም ከአዋጆቹ መውጣት በኋላ በአገር አቀፍም ሆነ በዓለም

አቀፍ ደረጃ በርካታ የኢኮኖሚ፣ የቴክኖሎጂ፣ የአደረጃጀትና የአሠራር ለውጦች በመኖራቸው አዋጆቹን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡ የዚህ አጭር ማብራሪያ ዓላማም አዋጆቹን መሻር ለምን እንዳስፈለገና የረቂቅ ሕጉ ዓላማ እና ግብ ምን እንደሆነ፣ ረቂቅ አዋጁ እንዴት እንደተዘጋጀ እንዲሁም በረቂቅ አዋጁ የተካተቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ማብራራት ነዉ፡፡

## 2. <u>አዋጁን በአዲስ መልክ ማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት</u>

ሀገራችን በጀመረችዉ አጠቃላይ ሀገራዊ የሪፎርም አጀንዳ ማዕቀፍ ዉስጥ የባንክ ዘርፍ ለዉጭ ኢንቨስተሮች ክፍት እንዲሆን የሚንስትሮች ምክር ቤት ነሐሴ 8 ቀን 2014 ውሳኔ አሳልፏል፡፡ በመሆኑም የዘርፉን አገልግሎት በዘመናዊ ዕዉቀት እና ቴክኖሎጂ ለመደገፍ፤ ከዓለም አቀፍ ገበያ ጋር ያለዉን ትስስር ለማጠናከር፤ የዘርፉን ተወዳዳሪነት፣ ዉጤታማነትና ቀልጣፋነት በማሳደግ በቂ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር እና የዉጭ ምንዛሪ አቅርቦት እንዲያድግ፤ የስራ ዕድል እንዲሰፋ፤ እንዲሁም ቀጣይነት ያለዉን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ እንዲቻል አዋጁን በአዲስ መልክ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

## 3. <u>የረቂቅ ሕጉ ዓላማ እና ግብ</u>

የተዘጋጀው ረቂቅ ህግ ዓላማና ግቦች፡

- አዳዲስ ባንኮች ወደ ባንክ ዘርፍ ሲቀላቀሉ ሊያሟሉ ስለሚገባዉ መስፈርት እና የፈቃድ አሰጣጥ ሂደት ለመወሰን፣ ፈቃድ አግኝተዉ ሥራ ከጀመሩ በኋላ ቅድመ ጥንቃቄን እና አደጋን መሠረት ያደረገ የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት ዘርግቶ ተከታታይነት ባለዉ አግባብ ተግባራዊ ለማድረግ፤ በአንድ ባንክ ላይ የፋይናንስ ቀዉስ በሚከሰትበት ጊዜ ባንኩ ከቀዉሱ እንዲወጣ እና እንዲያገግም ይህም ካልተቻለ በባንክ ዘርፍ እና በአጠቃላይ ኢኮኖሚዉ ላይ አለመረጋጋት ሳይፈጠር እንዲሁም የገንዘብ አስቀማጮች እና ሌሎች አበዳሪዎች ጥቅም ለከፍተኛ አደጋ ሳይጋለጥ የተለያዩ አማራጮች እና ስልቶችን በመጠቀም ባንኩ ከገበያ እንዲወጣ የሚደረግበትን ማዕቀፍ ለመዘርጋት፣
- የሀገራችን የባንክ ዘርፍ ለዉጭ ኢንቨስትመንት ክፍት እንዲደረግ በመንግሥት የተላለፈዉ የፖሊሲ ዉሳኔ ወደ ተግባር ለማሸጋገር እና የዉጭ ባንኮች እና ኢንቨስተሮች በዘርፉ ተሰማርተዉ ለኢኮኖሚዉ ቀጣይ ዕድገት የበኩላቸዉን አበርክቶ እንዲሰጡ የሚያስችል የህገ ማዕቀፍ ለመዘርጋት፣እና

- በአዲሱ የብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ ላይ ለብሔራዊ ባንክ ከተሰጡት ቁልፍ ተልእኮዎች መካከል አንድ ባንክ የፋይናንስ ቀዉስ ሲገጥመው ለተከሰተዉ ቀዉስ የእልባት ሰጪነት ሥልጣን እና ሀላፊነት (Resolution Authority) ይገኝበታል። በመሆኑም ብሔራዊ ባንክ የተለያዩ የመፍትሄ ስልቶችን እና አማራጮችን በመጠቀም ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉትን ዝርዝር የህግ ድንጋጌዎችን በተዘጋጀው ረቂቅ እንዲካተቱ ማድረግ ነዉ።

## 4. <u>የተከናወኑ ቅድመ ማርቀቅ እና ድህረ ማርቀቅ ተግባራት</u>

አዋጁን ለማርቀቅ እንዲረዳ በባንኩ ውስጥ የተቋቋሙ ቡድኖች፣ የሌሎች አገራትን ተሞክሮዎች ያካተተ የጥናት ሪፖርት አዘጋጅተዋል። የባንክ ዘርፍን ለዉጭ ኢንቨስትመንት ክፍት የማድረግን ጉዳይ በተመለከተ የአዋጁ ቅድመ ማርቀቅ ምዕራፍ አካል የሆነ የፖሊሲ ሰነድ በብሔራዊ ባንክ በኩል እንዲዘጋጅ ተደርጎ ነሐሴ 8 ቀን 2014 በተደረገዉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰነዱ ታይቶ ጸድቋል።

በመንግሥስት በጸደቀዉ የፖሊሲ ዉሳኔ መሠረት የተዘጋጀዉ ረቂቅ ሕግ በመጀመሪያ ዙር ከመንግስት እና ከግል ዘርፉ ተዋናዮች ማለትም ከባንኮች፣ ከመድን ሰጪ ድርጅቶች፣ ከአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት፣ ከፋይናንስ ሊዝ ኩባንያዎች፣ ከብሔራዊ ባንክ የሥራ ክፍሎች፣ ከዉጭ ባንክ ተጠሪ ቢሮዎችና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ዝርዝር የጽሑፍ አስተያየት የተሰበሰበ ሲሆን በመቀጠልም የባንክ ቦርድ ሰብሳቢዎችን ጨምሮ ከተወካዮቻቸዉ እንዲሁም ከሌሎች የፋይናንስ ተቋማት እና ተሳታፊዎች ጋር የምክክር መድረክ ተካሂዷል።

በመቀጠልም በመጀመሪያ ዙር የተሰጡ ግብዐቶችን እና አስተያየቶችን ባካተተዉ የተከለሰ ረቂቅ ህግ ላይ ከሚመለከታቸዉ የብሔራዊ ባንክ የዉስጥ የስራ ክፍሎች ጋር እንዲሁም ከባንኮች የስራ ሀላፊዎች ጋር ሁለተኛ ዙር የዉይይት መድረክ ተዘጋጅቶ ጠቃሚ ግብዐቶች የተወሰዱ ሲሆን በዚህም አግባብ የመጨረሻዉ ረቂቅ ህግ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

እንዲሁም ዓለም ባንክን ጨምሮ በዘርፉ ሰፊ ልምድና ተሞክሮ ያላቸዉ የልማት አጋሮች እና ባለሙያዎችም በየደረጃዉ ጠቃሚ ግብዓት እንዲሰጡ ተደርጎ ረቂቅ አዋጁ የበለጠ እንዲዳብር ተደርጓል። የአዋጁ ረቂቅ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ቦርድ ከጸደቀ በኋላ በፍትህ ሚኒስቴር ታይቶ የተሰጡ አስተያየቶች በረቂቅ አዋጁ እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 5. የረቂቅ አዋጁ ቅርጽ እና ይዘት

### 5.1 ቅርጽ

ረቂቅ አዋጁ በአጠቃላይ በአስራ አንድ ክፍሎች የተዋቀረ እና 94 አንቀጾችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል አጭር ርዕስ እና ትርጓሜ የተመለከቱ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን፤ ክፍል ሁለት ስለ ባንክ ሥራ ፈቃድ፣ ክፍል ሶስት የውጭ ዜጎች በባንክ ሥራ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ፤ ክፍል አራት ስለ አክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች ጉባኤ፤ ክፍል አምስት ስለ ባንክ ሠራተኞችና ዳይሬክተሮች፣ ክፍል ስድስት የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች፤ ክፍል ሰባት ስለ ፋይናንስ መዝገቦችና የውጭ ኦዲተር ሹመት፤ ክፍል ስምንት መረጃ ስለ መስጠት፣ ሪፖርት ስለ ማቅረብ እና በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ምርመራ፤ ክፍል ዘጠኝ ውህደት፣ ግዥ፤ እና ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲሁም ሀብት እና ዕዳ ስለ ማስተላለፍ፣ ክፍል አስር ስለ እልባት፣ ፈቃድ ስለ መሠረዝና ስለ መፍረስ የሚደነግጉ ሲሆን የመጨረሻው ክፍል አስራ አንድ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎችን የያዘ ነው፡፡

### 5.2 ይዘት

#### 5.2.1 የአዋጁ መግቢያ፡

ባንኮች ገንዘብ በማሰባሰብ እና ወደተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በማሰራጨት እንዲሁም በክፍያና የሂሳብ ማወራረድ ሥርዓት ውስጥ ያላቸዉን ወሳኝ ሚና በመግለጽ ነባሩን ሕግ መተካት ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁም የሕጉ ዓላማ ምን እንደሆነ ሊያሳይ በሚችል መልኩ ተቀምጧል፡፡ በጥቅሉ፣ በጥንቃቄ በተዘጋጀ የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ አማካኝነት የባንክ ዘርፍን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት የማድረግ፣ በፋይናንስ ቀዉስ ዉስጥ ለገባ ባንክ ከፍተኛ የሥርዓት መናጋት እና ኪሳራ በማያስከትል መልኩ እልባት መስጠት እንዲቻል ለብሔራዊ ባንክ የዕልባት ሰጭነት ሥልጣን እና ሀላፊነት የመስጠት እንዲሁም የባንክ ሥራን በቀጣይነት ጤናማ እና አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል የተሟላ፣ ወቅቱን የዋጀ እና ዓለም አቀፍ ልምዶችን እና አሰራሮችን ያገናዘበ የሕግ ማዕቀፍ የመዘርጋት አስፈላጊነት ተገልጿል፡፡

#### 5.2.2 ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

በዚህ ክፍል የተመለከተዉ የአዋጁ አጭር ርዕስ ‹‹የባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር ……./፪ሺ፲፮›› በሚል የተጠቀሰ ሲሆን፤ ይህም ከነባሩ አዋጅ ጋር ተመሳሳይነት ያለዉ ነዉ፡፡ ስያሜዉ ተመሳሳይ የሆነበት ምክንያትም እንደ ቀድሞው ሁሉ ይህ ስያሜ የተሻሻለዉን አዋጅ ሊገልጽ እና ሊያመላክት የሚችል በመሆኑ ነዉ፡፡

በተጨማሪም፣ የረቂቁ አንቀጽ 2 ትርጉም የተሰጣቸውን ቃላት እና ሐረጋት በውስጡ የያዘ ሲሆን፣ ከአዋጅ ቁጥር 592/2001 (በአዋጅ ቁጥር 1159/2011) ጋር ሲነጻጸር እንደ አዲስ የተተረጎሙ እና ትርጉማቸው የተሻሻለ ቃላትና ሐረጋትን አካቷል፡፡ ለምሳሌ “ግዢ”፤ “ሀብት እና ዕዳ ማስተላለፍ”፤ “የንብረት አስተዳደር ተቋም”፤ “ተጠቃሚ ባለቤት”፤ “የሽግግር ባንክ”፤ “የውጭ ባንክ”፤ “የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ”፤ “የውጭ ባንክ ተቀጥላ”፤ “የውጭ ሀገር እናት ባንክ"፤ “ውህደት”፤ “የሞግዚት አስተዳዳሪ”፤ “የሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፍ”፤ “ልዩ ባንክ”፤ “በሕግ አስገዳጅነት የሚፈጸም ውህደት”፤ “ስትራቴጂክ ኢንቬስተር”፣ “የማገገም ዕቅድ”፤ “እልባት”፤ “የእልባት እቅድ፤ “የእንደራሴ ቢሮ” እና የመሳሰሉት በተሻሻለዉ ሕግ በተለያዩ ቦታዎች በተደነገጉ አንቀጾች ጥቅም ላይ የዋሉ በመሆኑ አዲስ ትርጓሜ እንዲሰጣቸዉ ተደርጓል፡፡ በሌላ በኩል፣ “ከፍተኛ ሥራ አስፈጻሚ”፤ “ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ”፤ “ብድር”፤ “ባንክ”፤ “የባንክ ስራ”፤ “የፋይናንስ ተቋም” እና የመሳሰሉት ቃላትና ሐረጋት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱ ምክንያቶች ማለትም የባንክ ዘርፍን ለዉጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ከማድረግ ጋር ተያይዞ፣ ከባዝል ማዕቀፍ ጋር ለማጣጣም፣ የወለድ ነጻ ፋይናንስ አገልግሎትን ለማካተት እንዲሁም ትርጓሜዎቹ የበለጠ ግልጽ እና ገላጭ እንዲሆኑ በማስፈለጉ ምክንያት ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ በመጨረሻም “ዋና ሥራ አስፈፃሚ”፣ “ዳይሬክተር”፣ “የሂሣብ ዓመት”፣ “መደበኛ የሥራ ሂደት”፣ “ዕዳ መክፈል የማይቻልበት ወሰን”፤ “በዋስትና የተጠበቀ የይገባኛል ጥያቄ” እና የመሳሰሉት ቃላትና ሐረጋት ለዉጥ የማያስፈልጋቸዉ በመሆኑ አሁን ያላቸዉን ትርጓሜ ይዘዉ እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡

### 5.2.3 ክፍል ሁለት ስለ ባንክ ሥራ ፈቃድ

ይህ ክፍል ስለ ባንክ ሥራ ፈቃድ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን፣ የአዋጁን ዋና ይዘት ከያዙ ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ ይህ ክፍል በአብዛኛዉ በነባሩ አዋጅ የተካተቱ አንቀጾችን ያካተተ ሲሆን፣ በተለያዩ የአዋጁ አንቀጾች የሚከተሉትን ጉዳዮች ማለትም የባንክ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስላለበት መስፈርት፤ፈቃድ ለማግኘት ስለሚያስፈልጉ ቅድመ

ሁኔታዎች፤ፈቃድ ስለመስጠት፤ የባንክ ሥራ ስለመጀመር፤ የፈቃድ እድሳት፤ ፈቃድ የተሰጣቸውን ባንኮች ዝርዝር ስለማሳተም፤ እና ቅርንጫፍ ወይም ንዑስ ቅርንጫፍ ስለመክፈት የተመለከቱ ድንጋጌዎችን አካቷል፡፡

ሆኖም ይህን ክፍል በያዘዉ በተሻሻለዉ ረቂቅ አዋጅ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የሚሰጣቸዉ አካላት ለ"ባንክ" በተሰጠዉ ትርጓሜ መሠረት የዉጭ ባንክ ተቀጥላ፣ ወይም የዉጭ ባንክ ቅርንጫፍን የሚያካትት መሆኑ፤ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣዉ መመሪያ መሠረት ለውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ፈቃድ የሚሰጠው አካል ብሔራዊ ባንክ ስለመሆኑ እና አስቀድሞ ከሌላ የመንግሥት አካል ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም የውጭ ባንክ እንደራሴ ቢሮ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ መጠየቅ እና ማግኘት እንዳለበት፤ በተሻሻለዉ የንግድ ሕግ መሠረት አንድ ባንክ የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሁፉን ማስመዝገብ እንዳለበት እንዲሁም በባለ አንድ አባል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መልኩ የተቋቋመ የውጭ ባንክ በግል የሚሰጥ መግለጫ ማስመዝገብ እንዳለበት፤ አንድ ባንክ በመደበኛነት የባንኩን ተጠቃሚ ባለቤት የሆነውን የተፈጥሮ ሰዉ (Beneficial Owner) በመለየት ማሳወቅ እንዳለበት የሚደነግጉ ዋና ዋና አዳዲስ ድንጋጌዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 5.2.4 ክፍል ሶስት
## የውጭ ዜጎች በባንክ ሥራ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ

የውጭ ዜጎች በባንክ ሥራ ስለሚሳተፉበት ሁኔታ የተመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎች በዚህ ክፍል ተካትተዋል፡፡ ይህ ክፍል በነባሩ አዋጅ ያልነበረ እና የባንክ ዘርፍ ለዉጭ ኢንቨስትመንት ክፍት እንዲደረግ መወሰኑን ተከትሎ በተሻሻለዉ አዋጅ በአዲስ መልክ እንዲካተት የተደረገ ነዉ፡፡ ይህ ክፍል ጠቅላላ ድንጋጌዎችን፤የውጭ ባንክ ተቀጥላ በባንክ ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ፤የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ በባንክ ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ፤እና እንደራሴ ቢሮ ስለሚሠራው ሥራ የተመለከቱ ጉዳዮችን በውስጡ አካቷል፡፡

ይህ ክፍል ማንኛዉም የውጭ ባንክ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የሚይዘው የውጭ ባንክ ተቀጥላ እንዲያቋቁም ወይም የውጭ ባንክ ቅርንጫፍ እንዲከፍት ወይም እንደራሴ ቢሮ እንዲከፍት ወይም የባንክ አክሲዮኖችን እንዲይዝ ሊፈቀድለት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ የውጭ ባንክ ያልሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች ወይም በውጭ ሀገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የባንክ አክሲዮን እንዲይዙ ሊፈቀድ እንደሚችል ያስቀምጣል፡፡

ማንኛውም ስትራቴጂክ ኢንቨስተር በአንድ ነባር ወይም አዲስ የሀገር ውስጥ ባንክ የሚይዘው ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ከባንኩ አጠቃላይ የተፈረመ ካፒታል ከአርባ በመቶ መብለጥ እንደማይችል፤ ማንኛውም የውጭ ዜግነት ያለው እና እንደ ስትራቴጂክ ኢንቨስተር የማይቆጠር ግለሰብ ኢንቨስተር ወይም በውጭ ሀገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዘ የኢትዮጵያ ድርጅት በአንድ ነባር ወይም አዲስ የሀገር ውስጥ ባንክ የሚይዘው ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ከባንኩ አጠቃላይ የተፈረመ ካፒታል እንደ ቅደም ተከተሉ ከሰባት በመቶ እና ከአስር በመቶ መብለጥ እንደማይችል፡ በአንድ ባንክ ውስጥ የውጭ ዜጎች እና በውጭ ሀገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የሚይዙት አጠቃላይ የአክስዮን መጠን ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ከአርባ ዘጠኝ በመቶ መብለጥ እንደማይችል እንዲሁም ብሔራዊ ባንክ የዉጭ ባንኮችን በተመለከተ ቁጥራቸዉን እና የሚያደርጉትን የኢንቨስትመንት መጠን መወሰን ጨምሮ የተለያዩ ጉዳዮችን አስመልክቶ መመሪያ በማዉጣት መተግበር እንደሚችል የሚገልጹ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የተመለከቱ ድንጋጌዎች አካቷል፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች መንግሥት የባንክ ዘርፍን ለዉጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ማድረግን አስመልክቶ ከዚህ ቀደም ያጸደቀዉን የፖሊሲ ሰነድ መሠረት በማድረግ የተደነገጉ ድንጋጌዎች ሲሆኑ፣ አንዳንድ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲዉ ከጸደቀ በኋላ የተገኙ የዉጭ ሀገር ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት የተገኙ ተጨማሪ ግብዓቶችን በመዉሰድ መለስተኛ ማሻሻያ እና ተጨማሪ ድንጋጌዎች እንዲካተቱበት ተደርጓል፡፡ ከዚህ ቀደም ለስትራቴጂክ ኢንቨስተር የተሰጠዉን ትርጓሜ ሰፋ በማድረግ የተሻለ ካፒታል እና የባንክ እዉቀት እና ክህሎት ይዘዉ ሊመጡ የሚችሉ አካላትን ማለትም ዓለም አቀፍ የልማት ፋይናንስ ተቋማት እና የመሳሰሉት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ አንድ ስትራቴጂክ ኢንቨስተር በአንድ የሀገር ውስጥ ባንክ የሚይዘው ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ከሰላሳ በመቶ ወደ አርባ በመቶ ከፍ እንዲል፤ የውጭ ዜግነት ያለው ስትራቴጂክ ያልሆነ ግለሰብ ወይም ተቋም በአንድ የሀገር ውስጥ ባንክ የሚይዘው ቀጥተኛ የአክሲዮን ድርሻ ከዚህ ቀደም ከነበረው አምስት በመቶ እንደ ቅደም ተከተሉ ወደ ሰባት በመቶ እና አስር በመቶ ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ በአንድ ባንክ ውስጥ የውጭ ዜጎች እና በውጭ ሀገር ዜጋ በባለቤትነት የተያዙ የኢትዮጵያ ድርጅቶች የሚይዙት አጠቃላይ የአክስዮን መጠን ከአርባ በመቶ ወደ ከአርባ ዘጠኝ በመቶ ከፍ እንዲል እንዲሁም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በጉልህ ሊጠቅሙ የሚችሉ ስትራቴጂክ ኢንቨስትመንቶችን ለማምጣት እንዲሁም በቀዉስ ላይ ላለ ባንክ ዕልባት ለመስጠት እና የፋይናንስ መረጋጋትን ለማስጠበቅ

ብሔራዊ ባንክ ጥሩ የፋይናንስ መሠረት እና ስም ያለዉ የዉጭ ሀገር ባንክ አንድ ሥራ ላይ ያለን የሀገር ዉስጥ ባንክ በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ መጠቅለል እንዲችል በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ እንደሚችል የሚደነግግ ድንጋጌ በተጨማሪነት ተካቷል፡፡ እነዚህ መለስተኛ ማሻሻያ የተደረገባቸዉ ጉዳዮች የፖሊሲዉን አላማ የበለጠ ሊያሳኩ እንደሚችሉ የታመነባቸዉ አና የፖሊሲዉ ዋነኛ መሠረት የሆነውን የኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ በዋናነት በሀገር ዉስጥ ባንኮች እና ባለሀብቶች ተይዞ እንዲቆይ ማድረግን በሚያስጠብቅ መልኩ የተደረጉ ለዉጦች ናቸዉ፡፡

## 5.2.5 ክፍል አራት

## ስለ አክሲዮኖችና የባለአክሲዮኖች ጉባኤ

ይህ ክፍል የባንክ አክሲዮኖች እና የባለአክሲዮኖች ጉባኤ የተመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን፣ ማሻሻያ ከተደረገባቸዉ መጠነኛ የሕግ አንቀጾች ውጭ በአብዛኛዉ በነባሩ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነዉ፡፡ ይህ ክፍል የሚከተሉትን ጉዳዮች ማለትም ስለ አክሲዮኖች አይነት እና የአክሲዮን መዝገብ ስለሚያዝበት ሁኔታ፤ አክሲዮን የመያዝ ገደብ፤ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የብሔራዊ ባንክ ድርሻ ምን እንደሆነ፤ ድምፅ የመስጠት እና ሌሎች ኢኮኖሚያዊ መብቶች ስለሚገደቡበት ሁኔታ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን በውስጡ አካቷል፡፡ በዚህም በማንኛውም ባንክ ውስጥ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ ያለው አንድ ባለአክሲዮን ብሔራዊ ባንክ በመመሪያ የሚወስናቸውን የስነ-ምግባርና የተገቢነት መስፈርቶች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ብሔራዊ ባንክ የባለአክሲዮኑን ድምፅ የመስጠት መብት ከማገድ ባለፈ፣ ባለአክሲዮኑ በባንኩ ውስጥ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲኖረው ካስቻለው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ የተወሰነውን እንዲያስተላልፍ ሊያስገድድ እና አክሲዮኑ በዚህ መልኩ እስኪተላለፍ እና ሌሎች የተገኙ ጉድለቶች በአግባቡ እስከሚታረሙ ድረስ የትርፍ ክፍፍል እንዳይደረግ ሊያግድ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

## 5.2.6 ክፍል አምስት

## ስለ ባንክ ሠራተኞችና ዳይሬክተሮች

ይህ ክፍል ስለ ባንክ ሠራተኞችና ዳይሬክተሮች በተመለከተ አዳዲስ ሆነዉ እንዲገቡ እና ማሻሻያ የተደረገባቸዉን የተወሰኑ የሕግ አንቀጾች ከማካተት ውጭ በአብዛኛዉ በነባሩ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን፣ የሚከተሉትን ጉዳዮች ማለትም የውጭ ሀገር ዜጎች በባንክ ውስጥ ስለሚቀጠሩበት ሁኔታ፤ ከባንክ ሥራ አመራር ራስን ስለማግለል፤ ክልከላዎች፤

የዳይሬክተሮች እና የሥራ አስፈጻሚዎች ሹመት እና በብሔራዊ ባንክ ስለሚወሰድ የማገድና የማሰናበት እርምጃ በውስጡ አካቷል፡፡ ከእነዚህ መካከል የውጭ ሀገር ዜጎች በባንክ ውስጥ የሚቀጠሩበትን ሁኔታ በተመለከተ ልዩ እውቀት ወይም ሙያ በሚጠይቁ ቁልፍ የሥራ መደቦች ላይ ባንኮች የውጭ ሀገር ዜጎችን ከአምስት ዓመታት ላልበለጠ ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ በሚደረግ ውል እና ከብሔራዊ ባንክ በሚሰጥ ፈቃድ ሊቀጥሩ እንደሚችሉ፤ የቅጥር ጊዜዉ ከብሔራዊ ባንክ በሚሰጥ ልዩ ፈቃድ ለተጨማሪ አምስት ዓመት ሊራዘም እንደሚችል፣ ከላይ በተመለከተዉ አግባብ የተፈቀደዉ ጊዜ ሲያበቃ የሥራ መደቡ በኢትዮጵያ ዜጋ መተካት እንደሚኖርበት፤ ማንኛዉም ባንክ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ሰው ከመደበ በኋላ በቂ እና አጥጋቢ በሆነ መልኩ ለኢትዮጵያዉያን የእዉቀት እና የክህሎት ሽግግር መደረጉን ማረጋገጥ እንዳለበት እንዲሁም ማንኛዉም የውጭ ሀገር ዜጋ የሆነ ሠራተኛ ወይም ዳይሬክተር በብሔራዊ ባንክ የተቀመጡትን የአግባብነት እና የሥነ-ምግባር መስፈርቶች ሳያሟላ ከቀረ፤ በኢትዮጵያ የውስጥ የፖለቲካ ጉዳይ ላይ ተሳትፎ ከተገኘ እና/ወይም በማንኛውም የእምነት ማጉደል ወይም የማጭበርበር ወንጀል በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም በሌላ ሀገር ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ባንኩ ሠራተኛውን ወይም ዳይሬክተሩን ወዲያውኑ ከሥራ ማሰናበት እና ጉዳዩን ለብሔራዊ ባንክ ማሳወቅ እንዳለበት የሚደነግጉ ድንጋጌዎች በአዲስነት ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም፣ የባንክ ዳይሬክተሮች በተሻለ እዉቀት እና ዉጤታማ በሆነ መንገድ ሀላፊነታቸዉን እንዲወጡ እና የባንኩን አላማ እንዲያስፈጽሙ ለማስቻል ነጻ እና ገለልተኛ የሆኑ ግለሰቦችን (Independent Directors) በቦርድ ዉስጥ ማካተት እንዳለባቸዉ የሚያስገድድ ድንጋጌ በአዲስነት ተካቷል፡፡

## 5.2.7 ክፍል ስድስት

## የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች

ይህ ክፍል የፋይናንስ ግዴታዎችና ገደቦች በተመለከተ በውስጡ ባንኮች ተፈላጊውን ካፒታል፤ ሕጋዊ የመጠባበቂያ ሂሣብ እንዲሁም በቂ ገንዘብ አከል ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ እንዲሁም ፕሮቪዥንና የእርጅና ቅናሽ መያዝ እንዳለባቸዉ እና ባንኮች ኪሳራ የመሸፈንና የማጣጣት ግዴታዎች እና በአንዳንድ የባንክ አገልግሎቶች ላይ የሚጣሉ ገደቦችን የተመለከቱ የህግ ድንጋጌዎችን ያካተተ ሲሆን እነዚህ ድንጋጌዎች በአብዛኛዉ በነባሩ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የያዙ እና ጉልህ ማሻሻያ ያልተደረገባቸዉ ናቸዉ፡፡ ሆኖም የገንዘብ አከል ንብረት

ተብለዉ የሚካተቱ የንብረት አይነቶችን ዝርዝር በተመለከተ ባንኮች ካላቸዉ ጥሬ ገንዘብ እና በብሔራዊ ባንክ ተቀማጭ ካደረጉት ዉጭ ያሉ ሌሎች ንብረቶች ብሔራዊ ባንክ በየጊዜዉ በሚወስነዉ መሰረት እንደሚካተቱ በሚገልጽ መልኩ የተሻሻለ ሲሆን ባንኮች በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አደራረግ ደረጃ መሰረት ተጨማሪ የመጠባበቂያ ገንዘብ ሊይዙ እንደሚችሉ የሚፈቅድ አዲስ ድንጋጌ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

## <u>5.2.8 ክፍል ሰባት</u>
## <u>ስለ ፋይናንስ መዝገቦችና የውጭ ኦዲተር ሹመት</u>

ይህ ክፍል የዉጭ ኦዲት ሪፖርት በተመለከተ በውስጡ ባንኮች መያዝ ስላለባቸዉ የፋይናንስ መዝገቦች፤ የዉጭ ኦዲተሮች ስለሚሾሙበት አግባብ እንዲሁም ስለ ፋይናንስ መዝገቦችና የውጭ ኦዲተር ሹመት የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካተተ ሲሆን፣ እነዚህም በአብዛኛዉ በነባሩ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የያዙ ናቸዉ፡፡ ሆኖም፣ ብሔራዊ ባንክ የአንድን ባንክ የዉጭ ኦዲተር ሹመት በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም ነጻ እና ገለልተኛ ሆኖ ካለመገኘት፤እንዲሁም የታወቁ ሙያዊ አሠራሮችን ካለመከተል ጋር በተያያዘ መሰረዝ የሚያስችለዉ ሥልጣን እንዲኖረዉ ዓለም አቀፍ ልምድ እና ተሞክሮን መሠረት በማድረግ በረቂቅ አዋጁ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

## <u>5.2.9 ክፍል ስምንት</u>
## <u>መረጃ ስለ መስጠት፣ ሪፖርት ስለ ማቅረብ እና በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ምርመራ</u>

ይህ ክፍል መረጃ ስለ መስጠት፣ ሪፖርት ስለ ማቅረብ እና በባንኮች ላይ የሚካሄድ ምርመራን በተመለከተ የተለያዩ ድንጋጌዎችን ያካተተ ሲሆን፣ እነዚህም በአብዛኛዉ በነባሩ አዋጅ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን የያዙ ናቸዉ፡፡ በዚህ ክፍል ሪፖርት ስለ ማቅረብ እና መረጃ ስለ መስጠት፣ በባንኮች ላይ ስለሚካሄድ ምርመራ፣ የምርመራ ሪፖርት ስለሚዘጋጅበት እና አስቸኳይ የማስተካከያ እርምጃዎች ስለሚወሰድበት አግባብ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ በተለይ ምርመራን መሠረት በማድረግ ባንኮች ላይ በብሔራዊ ባንክ ሊወሰዱ የሚችሉ የማስተካከያ እርምጃዎችን በተመለከተ በተዘጋጀዉ ረቂቅ አዋጅ ሰፋ ባለ መልኩ በማየት በነባር አዋጁ ከተጠቀሱ እርምጃዎች በተጨማሪ ሌሎች ዘርዘር ያሉ አዳዲስ የእርምጃ አይነቶችን አካቷል፡፡

## 5.2.10 ክፍል ዘጠኝ
## ውህደት፣ ግዥ፤ እና ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲሁም ሀብት እና ዕዳ ስለማስተላለፍ

ይህ ክፍል ባንኮች ውህደት ስለሚያከናውኑበት፤ ግዥ፤ እና ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻ እንዲሁም የባንኮች ሀብት እና ዕዳ ስለሚተላለፍበት አግባብ የተመለከቱ ጉዳዮችን በውስጡ አካቷል። ብሔራዊ ባንክ አንድ ባንክ ላይ የፋይናንስ ቀዉስ ሲደርስ ለተከሰተዉ ቀዉስ መፍትሔ እና እልባት እንዲሰጥ የማድረግ ሥልጣን እና ሀላፊነት (Resolution Authority) የተሰጠዉ መሆኑን ተከትሎ በዚህ ክፍል የተካተቱ ድንጋጌዎች በነባሩ አዋጅ የሌሉ እና እንደ አዲስ የተካተቱ የሕግ ድንጋጌዎች ናቸዉ። በዚህ ክፍል በተደነገጉ የተለያዩ አንቀጾች ከብሔራዊ ባንክ በቅድሚያ የጽሑፍ ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛዉም ባንክ በፈቃደኝነት ውህደት መፈጸም እንደማይችል፤ ብሔራዊ ባንክ ችግር ያለባቸው ባንኮችን ለማዳን እና/ወይም ይበልጥ ጠንካራ የሆኑ ባንኮች እንዲፈጠሩ ለማስቻል በአስገዳጅነት የሚደረግ ውህደት እንዲፈጸም ማድረግ እንደሚችል፤ በአንድ ባንክ ወሳኝ የባለቤትነት ድርሻን የሚፈጥር ማንኛውም የአክሲዮን ዝውውር ወይም ግዥ በአክሲዮን መዝገብ ላይ ከመመዝገቡ በፊት በብሔራዊ ባንክ መጽደቅ እንዳለበት እንዲሁም በመደበኛ የሥራ ሂደት ካልሆነ በስተቀር ከብሔራዊ ባንክ አስቀድሞ የጽሑፍ ፈቃድ ሳይሰጥ ማንኛዉም ባንክ ሀብቱን ወይም ዕዳውን ለሌላ ባንክ ሊያስተላልፍ እንደማይችል በረቂቅ አዋጁ ተካቷል።

## 5.2.11 ክፍል አስር
## ስለ እልባት፣ፈቃድ ስለ መሠረዝና ስለ መፍረስ

ይህ ክፍል ጤናማ ያልሆነ የፋይናንስ አቋም ወይም ቀዉስ ላይ ላለ ባንክ እልባት ስለ መስጠት፣ የባንክ ፈቃድ ስለሚሰረዝበት አግባብ እና ባንክ ስለ ማፍረስ የተመለከቱ ጉዳዮችን በውስጡ አካቷል። በዚህ ክፍል ከተካተቱ ድንጋጌዎች ውስጥ በነባሩ አዋጅ የሌሉ እና ብሔራዊ ባንክ አንድ ባንክ ላይ የፋይናንስ ቀዉስ ሲደርስ ለተከሰተዉ ቀዉስ መፍትሔ እና እልባት እንዲሰጥ የማድረግ ሥልጣን እና ሀላፊነት (Resolution Authority) የተሰጠዉ መሆኑን በማስመልከት በአዲስ መልክ የገቡ የተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎች አካቶ ይዟል።

በዚህ ክፍል ከተካተቱ በርካታ የሕግ ድንጋጌዎች መካከል ባንኮች ሊመጣ የሚችል የፋይናንስ ችግር ከወዲሁ በመገመት ራሳቸዉ የማገገም ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበር እንደሚገባቸዉ፤ ብሔራዊ ባንክ በባንክ ሥርዐቱ ውስጥ ወሳኝ እና ጉልህ ድርሻ ባላቸዉ ባንኮች እና ሌሎች

ባንኮች ላይ የፋይናንስ ቀዉስ ቢከሰት በምን አይነት አግባብ እና ሁኔታ (ስትራቴጂ) ዕልባት ሊሰጥ እንደሚችል የሚያመለክት የእልባት ዕቅድ እንደ ቅድመ ጥንቃቄ አስቀድሞ ማዘጋጀት እና ቀዉሱ ሲከሰት ዕቅዱን መተግበር እንደሚኖርበት፣ አንድ ባንክ ላይ የፋይናንስ ቀዉስ ወይም ችግር ሲደርስ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ኮሚቴ ተዋቅሮ እና የአደጋ እና ቀዉስ አመራር ሥርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ ስለሚደረግበት አግባብ፣ ብሔራዊ ባንክ ችግር ላይ ላለ ባንክ የሞግዚት አስተዳዳሪ ስለሚሾምበት አግባብ፣ እንዲሁም ለሞግዚት አስተዳዳሪነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ የአገልግሎት ዘመን፤ የሚከፈል ክፍያ እና የሞግዚት አስተዳደር ወጪዎች አሸፋፈን፣ የሞግዚት አስተዳዳሪ ሥልጣን እና ተግባራት፣ የሞግዚት አስተዳዳሪ መሾምን በመቃወም ስለሚቀርብ አቤቱታ፣ በሞግዚት አስተዳዳሪ ላይ ስለሚደረግ የበላይ ቁጥጥር የተመለከቱ ጉዳዮችን እንዲሁም የትርፍ ክፍፍል ማገድን ጨምሮ ሌሎች መብቶችን ስለማገድ እንዲሁም የሞግዚት አስተዳዳሪው ስላሉት ባንኩን መልሶ የማቋቋሚያ አማራጮች የተመለከቱ የሕግ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም በረቂቅ አዋጁ ክፍል አስር በዋናነት ለፈቃድ ስረዛ ስለሚያበቁ ጉዳዮች፣ የመፍረስ ውሳኔ የተላለፈባቸዉ ባንኮች በተመለከተ የንብረት አጣሪ በመሾም የንብረት ማጣራቱ ተግባር ስለሚከናወንበት ሁኔታ፣ ባንክ ሲፈርስ በቅድሚያ ስለሚፈጸሙ ሥርዓቶች፣ በይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ስለሚሰጥ ውሳኔ፣ ስለተፈቀዱ የይገባኛል ጥያቄዎች የመጨረሻ ኘሮግራምና ድልድል እና የአከፋፈል ቅደም ተከተል፣ በፈቃደኝነት ስለሚከናወን የባንክ ማፍረስ ዉሳኔ አተገባበር፣ እና ስለንብረት የማጣራት ተግባር መጠናቀቅ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ምንም እንኳን ከባንክ መፍረስ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በነባሩ አዋጅ የተካተቱ ቢሆንም፣ ከላይ በቀረበዉ አግባብ ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የተካተቱት ድንጋጌዎች በአዲስ መልክ በረቂቅ አዋጁ የተካተቱ ናቸዉ፡፡

<u>5.2.12 ክፍል አስራ አንድ</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

የረቂቁ የመጨረሻው ክፍል የሆነው ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ሲሆን፣ ከላይ ባሉት ክፍሎች ውስጥ ሊካተቱ የማይችሉ የተለያዩ ጉዳዮችን በአንድ አቅፎ እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ብሔራዊ ባንክ ባንኮች ተቀጥላ ስለሚያቋቁሙብት እና ለልዩ ባንኮች ፈቃድ ስለሚሰጥበት እና ቁጥጥር ስለሚደረግበት አግባብ መመሪያ ሊያወጣ እንደሚችል፣ ዕዳ

መክፈል በማይቻልበት ወሰን ላይ ስለደረሰ ባንክ፣ የባንክ ባልሆኑ ሥራዎች ስለ መሰማራት፣ ባንኮች ስለሚያደርጉት የምርመራ አገልግሎት ክፍያ፣ የይገባኛል ጥያቄ ስላልቀረበባቸው ተከፋይ ሂሳቦች፣ የደንበኞችን ማንነት ስለማወቅ፣ የባንኮችና የመድን ኩባንያዎች ግንኙነት፣የደህንነት እርምጃዎች እና የመረጃ አስተዳደር፣ በቋሚ ንብረቶች እና በፋይናንስ ሀብት ላይ በባንኮች ስለሚደረግ ኢንቨስትመንት፣ በባንክ ስለሚደረግ ማስታወቂያ ስለማሳተም እና ስለማስነገር፣ በብድር እና በውጭ አገር ገንዘብ ላይ ስለሚጣል የፖርትፎሊዮ ድልድል ገደብ፣ ድንበር ተሻግሮ ስለመበደር፣ ስለማበደር እና ኢንቨስት ስለማድረግ፣ የባንክ ሥራዎችን በውጭ አካላት ስለማሠራት፣ የባንክ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች ምቹና ተደራሽ ስለማድረግ፣ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት፣ ለፋይናንስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለሚደረግ ጥበቃ፣ ከውጭ ሀገር ተቆጣጣሪ አካላት እና ከሀገር ውስጥ ባለሥልጣን አካላት ጋር ተባብሮ እና ተቀናጅቶ ስለመሥራት፣ ዓለም አቀፍ የባንክ ሥራ ቁጥጥር መርሆዎችን እና ደረጃዎችን በሥራ ላይ ስለማዋል፣ መረጃዎችን እንዲታተሙ ስለማድረግ፣ የብሔራዊ ባንክ ባልደረባዎች እና ተጠሪዎች ከግል ተጠያቂነት ስለሚጠበቁበት አግባብ፣ የሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፍ ተግባራዊ ስለማድረግ፣ ቅጣት፣ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ፣ የማቆያ ድንጋጌ፣ የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች እንዲሁም በመጨረሻ አዋጁ የሚፀናበት ጊዜን የሚደነግጉ ናቸው፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች ከፊሎቹ በነባሩ አዋጅ የተካተቱ ሲሆኑ፣ ከፊሎቹ ደግሞ ለምሳሌ፣ የሙከራ የቁጥጥር ማዕቀፍ ተግባራዊ ስለማድረግ፣ በብድር እና በውጭ አገር ገንዘብ ላይ ስለሚጣል የፖርትፎሊዮ ድልድል ገደብ፣ ድንበር ተሻግሮ ስለመበደር፣ ስለማበደር እና ኢንቨስት ስለማድረግ፣ ከውጭ ሀገር ተቆጣጣሪ አካላት እና ከሀገር ውስጥ ባለሥልጣን ጋር ተባብሮ እና ተቀናጅቶ ስለመስራት የመሳሰሉት በአዲስ መልክ በረቂቅ አዋጁ የተካተቱ ናቸዉ፡፡ በተለይም የባንክ ሀላፊዎች ክፍያ መርህን የተከተለ እና አሰራር ያለዉ፣ ግልጽ እና ተጠያቂነት ያለዉ እንዲሁም ባንኮቹን ላልተፈለገ አደጋ የማያጋልጥ እንዲሆን የሚያስችል አሰራር እንዲተገበር የሚያደርግ መመሪያ በብሔራዊ ባንክ እንደሚወጣ እና የወለድ አልባ የፋይናንስ አገልግሎት የሸሪአን መርህ በተከተለ መልኩ መሰጠት መቻሉ አገልግሎቱን ከሚሰጡ የፋይናንስ ተቋማት ጤናማነት እና ከአጠቃላይ የፋይናንስ ዘርፍ መረጋጋት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ይህን የሚያረጋግጥ ማዕከላዊ የሸሪአ ቦርድ ማቋቋምን ጨምሮ አጠቃላይ ከሸሪአ

አስተዳደር ጋር የተያዘዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ብሄራዊ ባንክ በጥናት ተመስርቶ መመሪያ በማውጣት ተግባራዊ እንደሚያደርግ የሚገልጹ ድንጋጌዎች በረቂቅ አዋጁ ተካተዋል፡፡

## 5.3 በረቂቁ እንዳይካተቱ የተደረጉ ድንጋጌዎች

በመጨረሻም በአዋጅ ቁጥር 592/2000 እና የባንክ ሥራ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1159/2011 ተካተው የነበሩ በረቂቁ እንዳይካተቱ የተደረጉ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ መሠረታዊ የሚባሉት የዉጭ ሀገር ዜግነት ያለዉ ትዉልደ ኢትዮጵያዊ በባንክ ሥራ ስለሚሳተፍበት ሁኔታ በተመለከተ በዝርዝር የተካተቱ ድንጋጌዎች እና በረቂቅ አዋጁ ከተጠቀሰዉ "Officail Adminstration" ሥልጣን እና ተግባራት ጋር የማይጣጣሙ ድንጋጌዎች ከረቂቁ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

ሌሎች ተጨማሪ ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ይህ ረቂቅ አዋጅ ሲዘጋጅ በመንግሥት በጸደቀዉ የፖሊሲ ሰነድ መሠረት የባንኩን ዘርፍ ለዉጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ማድረግን እና አንድ ባንክ ላይ የፋይናንስ ቀዉስ ሲደርስ ለተከሰተዉ ቀዉስ መፍትሔ እና እልባት እንዲሰጥ ለብሔራዊ ባንክ የተሰጠዉን የእልባት ሰጪነት ሥልጣን (Resolution Authority) ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉ የሕግ ድንጋጌዎችን ማካተት በዋነኝነት ታሳቢ አድርጓል፡፡ ከላይ በመግቢያ እንደተጠቀሰዉ፣ አዋጁን የማርቀቅ ሂደት ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደ ሲሆን፣ ሰፊ ጥናት በማድረግ የተለያዩ ዓለም አቀፍ መርሆችና ምርጥ ተሞክሮዎችን በመዉሰድ፣ እንዲሁም በተለያዩ አካላት የተሰጠ የቴክኒክ እገዛ መሰረት በማድረግ አዋጁን ለማርቀቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም፣ የአዋጁ ረቂቅ በሁለት ዙር ከባለድርሻ አካላት ጋር ዉይይት የተደረገበት እና የተለያዩ ጠቃሚ ግብዓቶች የተካተቱበት፣ በብሔራዊ ባንክ ቦርድ ደረጃ ዉይይት ተደርጎበት የጸደቀ ነው፡፡ በመቀጠልም፣ ረቂቁ በፍትህ ሚኒስቴር ታይቶ ግብአት እና አስተያየት እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን፣ የተሰጡ አስተያየቶች በረቂቅ አዋጁ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም፣ ይህ ረቂቅ ቀጣይ በሚደረጉ የአዋጅ ማጽደቅ ሂደቶች ዳብሮ ሲጸድቅ የባንክ ዘርፍን የቀጣይ ዓመታት አሠራር የበለጠ ጤናማ እና የተረጋጋ እንዲሆን በማስቻል ዘርፉ ለኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት መረጋገጥ የበኩሉን ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይታመናል፡፡